# <u>አዲስ ዓመት ስንቀበል</u>

ከቀመሩ ደሳለኝ

አዲስ ዓመት ስንቀብል እናመስግ ፈጣሪን
ጊዜ_ አመትን ባርኮ ላሳለፈው ላሸጋገረን
ቀን ወራት፣ ዓመታትን ላቀደልን
ጊዜን ፈቅዶ በቸርነቱ ለለገሰን
እናመስግን አምላክን ለዚህ ስጦታው ላበቃን ።

ጌታ ይመስገን ክብሩ ይስፋ ለዚህ ወቅት
ለስዓት ቀን ወር ዓመታት
ለጠበቀን በሰላም ዓመት ሙሉ በቸርነት
ላቀደልን ሁሉን አመቻችቶ በትዕግሥት
ኢትዮጵያን ይባርክ ለዘመናት ያኑራት
ይቁም ጌታ ከሕዝቧ ፊት ይጠብቃት
ምኞቴ ነው ጸሎቴ በዚህ አዲስ ዓመት።

አምላክ ያጠንክር የኢትዮጵያ ክንዶችዋን
ወደ እርሱ ወደ እግዚአብሔር የተዘረጉ እጆችዋን
የልቧን ፍቅር ያበርታ የእምነትዋን ቃል ለጌታ
ይስማ ልመናዋን የተማጸነችውን በአለኝታ
ፈቃዱ ይሁን ይደረግ ለሽግግር በደስታ።

በአለፈው ዓመት በአሮጌው ጊዜ ያላደረግነው
በሄደው ዓመት ያላነሳነው ያልሰራነው
በወጣው ዓመት ያላየነው ያልተመለከትን
እግዚአብሔር ርዳን ሃሴትን አድርግልን
ትናንት ያልሆነው ዛሬ ይሁን
አቀናጀው ዓመቱን ፍረድልን እውነት፣ መልካሙን።

አምላክ አዳምጥ ስማ ጩኸት
የሕዝብህን  ጭንቅ ብሶት
ፍትህ ላጡ የእምነት መብት ነፃነት
ሕዝብህን ባርክ በፊትህ የተደፋውን በጸሎት።

አምላክ ሆይ ዓይኖቻችንን ወደ አንተ እናቀናለን
የአንተን ስም ለሚያወድሱ ተመልከት ገዳማቱን
አፈር  ልሰው፣ ቅጠል በልተው ያሉትን
የሌሎችምን ተማጽኖ ጾም ጸሎታቸውን

አዳምጥ፣ ስማ  የሕዝብን ብሶት ጩሆቱን
እስከ መቼ ጌታ ሆይ ! አጥፋለት ጠላቱን።

በመለስ  በጳውሎስ አምና እንዳየነው
ባንዳውን ሁሉ በመለኮታዊ ኃይልህ ቀንጥሳቸው
ለኢትዮጵያ ስትል ሁሉንም አጥፋቸው።

የኢትዮጵያን ትንሣኤ ዘንድሮ እናያለን
ስለሆነም አምላክ ሆይ በአንተ እንተማመናለን።

መስከረም  2006 ዓ ም